# ኦህዴድና ብአዴን ከኢህአዴግ እና ከቆሙለት ሕዝብ መካከል አንዱን መምረጥ አለባቸው

[በወንድወሰን ተክሉ-ጋዜጠኛ]

**መነሻ-ወቅታዊው የኢህአዴግ ሁኔታ-

ኢህአዴግ ለሁለት በተከፈለበት በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ህዝባዊው ትግል እለት በእለት እየጠነከረ ሲቀጥል ይስተዋላል።

ሁለቱም ሃይሎች እያደረጉት ያለውን የህልውና ትንቅንቅ ወሳኝ በሆነ ታሪካዊ ምእራፍ ላይ እንደደረሰ ማየት ቢቻልም በኢህአዴግ በኩል አስኳሉ በሆነው ህወሃት ድርጅታዊ ህልውናውን ለመታደግ ውስጠ ድርጅታዊ ትግሉን እያጧጧፈ ያለበት ወቅት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በህዝባዊው ትግል ተጽእኖ  ፈጣሪነት በኢህአዴግ ውስጥ የተለየ አጀንዳ ይዘው በቀረቡት ኦህዴድና ብአዴን በአንድ ጎራ በሌላ በኩል በህወሃት የበላይነት ላይ አንዳችም ጥያቄ የሌለው ደህዴህና ህወሃት በሌላ ጎራ ሆነው የህወሃትን የበላይነት ለማስቀምና ለማስቀጠል እያካሄዱት ባለው ድርጅታዊ ትግል ውጤት እየተካሄደ ባለው ሕዝባዊው ትግል ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ ስለሚያሳርፍ ሂደቱን በቅርበትና በጥልቀት ለማየት የምንገደደው።

ሀገሪቷ መሪ አልባ ከሆነች የሰነባበተ ቢሆንም በስልጣን ላይ ያለው ገዢው ኢህአዴግ ከመቼውም ግዜ በላይ የመግዛት አቅሙና ብቃቱ ተንኮታኩቶ የታየበት ግዜ ቢኖር አሁን ያለበት ወቅት እንደሆነ ግልጽ ነው።

በድርጅቱ የስራ አስፈጻሚ ዝግ ስብሰባ ላይ ከአራቱ የድርጅቱ መስራቾችና አባል ድርጅቶች የቀረበው አጀንዳ ድርጅቱን ለሁለት ከመክፈሉም ባሻገር ህልውናውንም የሚያከትም ሁኔታዎችን እንዳካተተ ይታያል።

በስብሰባው ላይ የመከራከሪያ እና የመለያያ ዋና አጀንዳ በሀገሪቷ ውስጥ ለተነሳው ህዝባዊ ዓመጽ መንስኤ የህወሃት የበላይነት የፈጠረው ነው በሚሉት ኦህዴድና ብአዴን እና የለም የአመራር ድክመት የፈጠረው ነው በሚለው ህወሃት መካከል አሸናፊ ሀሳብ ወጥቶ የበላይነቱን ሲይዝ እስካሁን አልታየም።

ህወሃት ወደ ኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ላይ ከመታደሙ ሳምንታት በፊት በመቀሌ ባካሄደው ድርጅታዊ ሹምሽርና ለሳምንታት በፈጀው ግምገማን እንደ የመደራደሪያ ነጥብ በመጠቀም በኢህአዴግ ውስጥ ካሉት አራቱ ድርጅቶች ውስጥ እራሱን ለውጦና አሻሽሎ የቀረበው ብቸኛ ድርጅት ህወሃት ነው በማለት በኢህአዴግ ውስጥ ያለውን የአንበሳ ድርሻ ያለቅዋሜ መጫወት ይገባኛል ባይ እንደሆነ መረዳት ተችላል።

በእርግጥ አራቱም ድርጅቶች ይህን የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ላይ ከመታደማቸው በፊት በየፊናቸው ድርጅታዊ ግምገማዎችን አካሂደው የቀረቡ ቢሆንም ህወሃት በወሰድኩት የሹም ሽር እርምጃ እርምት አድርጌ የቀረብኩ ብቸኛው ድርጅት ነኝ በማለት ከኦህዴድና ብአዴን በኩል የቀረበበትን የህወሃት የበላይነትን ላለመቀበል ድርጅቶቹን በሚቻለው መጠን በማሸማቀቅና በማስፈራራት ሊደፍቅ ሲጥር ተስተውላል።

በድርጅቱ አፈቀላጤ አቶ ሺፈራው ሽጉጤ በኩል ስብሰባው ሳይጠናቀቅ የተጨነቁ የድርጅቱን አባላት ለማረጋጋት ታስቦ በተነገረው መግለጫ ውስጥ ድርጅቱ "በአዘቅት ውስጥ የተዘፈቀ" መሆኑን ሳይሸሽግ የገለጸ ሆኖ ሳለ በአንጻሩም የስብስባውን ፍጻሜ በድል እንደሚጠናቀቅ መተንበዩና ብሎም "በኢህአዴግ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የተለየ ውሳኔ እንወስናለን"ማለቱ አነጋጋሪ ብቻ ሳይሆን አስገራሚና አወዛጋቢም አባባል እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ለመሆኑ ህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ምን አዲስ ሊገኝ ይችላል? በእውኑ ከህወሃትስ አዲስ ነገር ማየትና መስማት የሚቻል ነውን?

መቼም ቢሆን ባለበቅሎ አርሶ አደር ለሰከንድም ቢሆን በቅሎይቱ ትወልዳለች ብሎ እንደማይጠብቅ ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም ለ27ዓመታት በጠመንጃ ሃይል እየገዛቸው ካለው ህወሃት አንዳች ረብ ያለው ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ አዲስ ነገር ከህወሃትና ከህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ይገኛል ብለው እንደማይጠብቁ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ የሚያውቀው እውነታ ነው።

ይህ እውነታ የተጠበቀ ሆኖ ሳለም ድርጅቱ[ህወሃት ማለቴ ነው] "እነሆ አዲስ ነገር አምጥቻለሁ" በማለት በቀጣይ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገዛበትን ያረጀና ያፈጀ ግን "አዲስ"ተብሎ የሚገለጽ ተግባራትን ፈጽሞ ብቅ ለማለት ውስጣዊ ስራ ላይ እንዳለ መረዳት ይኖርብናል።

**በኢህአዴግ ታሪክ ታይቶ የማይታወቀው ድርጅታዊ ውሳኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥያቄ መመለስ የሚያስችለው ነውን?

ወደ ሶስተኛ ዓመቱ እየተዳረሰ ያለው ሀገር አቀፉ ህዝባዊ ዓመጽና ጥያቄ በጉልህ ያስቀመጣቸው ወሳኝ ጥያቄዎችን ስናይ ኢህአዴግ አሁን ባለበት ደረጃ እና ህወሃት እራሴን አድሻለሁ በሚለው አቋሙ አንጻር ከቶም ቢሆን መመለስ የሚቻላቸው ጥያቄዎች እንደሆኑ ማወቅ ይቻላል።

ህዝባዊው ትግል ካነሳቸው ወሳኝ ጥያቄዎች ውስጥ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል-

1ኛ፡ የህወሃት የበላይነት ሳይሆን የሕግ የበላይነት ይስፈን

2ኛ-ፍትሃዊ የሀብት፣የስልጣንና የስራ ክፍፍል ይኑር

3ኛ-ተፈጥሮአዊ መብቶች፣የመደራጀት፣ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣በነጻነት በሁሉም የሀገሪቷ ግዛት ውስጥ የመስራትና የመንቀሳቀስ መብት ሳይሸራረፍና ሳይገደብ ይከበር።

4ኛ-የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ፣የህዝብን ሀብት ያላግባብ የመዘበሩ፣ንጹሃንን በግፍ የገደሉና ያሰቃዩ ለፍርድ ይቅረቡ

5ኛ-ሁሉን አቀፍ መንግስት ይመስረት ዘንድ ስርዓቱ ፈርሶ የሽግግር መንግስት ይቋቋም የሚሉት ከበርካታ የዓመጽ መንስኤዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ግን ወሳኝ የተባሉ ጥያቄዎች እንደሆኑ እናውቃለን።

"ታድሻለሁ" የሚለው ህወሃትም ሆነ አሁን በህወሃት የበላይነት የሚመራው ኢህአዴግ የቱንም ያህል ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ እርምጃና ማሻሻያዎችን አድርጌያለሁ ብሎ ቢቀርብም ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ከአንዱም ጋር ስምምነትን ፈጥሮ ተቀብሎ ይመልሳል ብሎ መጠበቅ አይደለም ማሰብ እንኳን የሚቻል አይደለም።

ህወሃት በውስጠ ድርጅቱ ያደረገውን ሹምሽር የተሃድሶዎች ሁሉ ቁንጮ ነው በማለት ሲፎልል ይሰማል።

ድርጅቱ በቀጣይ በኢህአዴግና በሀገሪቷ ላይ የመሪነትን ሚናን ያለቅዋሜ ለመጫወት መዘጋጀቱን ቢገልጽም እውነታው ግን ድርጅቱ እንደሚያወራው የተሻለ አመራርና የተለየ አይዲኦሎጂ ይዞ የተገኘ እንዳልሆነ ታይታል።

በአንጻሩም ድርጅቱ በባሰ ሁኔታ አቅመ ቢስና ሀሳበ ድኩማን የሆኑ አመራሮችን ይዞ በመቅረቡ የኢህአዴግን ተንኮታኩቶ መፍረስን የሚያበስር እንጂ የህዝቡን ጥያቄ በመመለስ የሚያረጋጋ ተራማጅ ሃይል እንደሌለው ታይቷል።

**ከብአዴን እና ኦህዴድ የሚጠበቀው ቀጣዩና ወሳኝ እርጃ ከተወሰደ ብቻ አዲስ ምእራፍ ሊታይ ይችላል-

ህወሃት ባለፈው ሳምንት መግባደጃ ላይ ያሳየውን የመለማመጥና ጥፋቶቹን የማመን አቀራረብ ስልታዊ ግን የማይተገበር የሆነ ነው ስል ባባለፈው ጽሁፌ አስፍሬ የነበረበት ቀለም ሳይደረቅ ሰሞኑን ወደ ቀደመ ማንነቱ በመመለስ አህዴድን እና ብአዴንን በዛቻ፣በማስፈራራትና በማሸማቀቅ የህወሃት የበላይነት ከሚሉት አቋማቸው እንዲፈናቀሉ ማስጨነቅ መጀመሩ ተሰምቷል።

ድርጅቱ[ህወሃት] እነዚህን የህዝብ ጥያቄ ይዘው መንቀሳቀስ የጀመሩትን ሁለት ድርጅት አመራሮች ለመምታትና በእነሱ እግር ተጋላቢ የሚሆኑ ታማኝ አገልጋዮችን ለመተካት መወሰኑ ታውቃል።

ሆኖም ይህን ውሳኔውን ገቢራዊ ለማድረግ በስብሰባ ላይ ያሉትን የሁሉትን ድርጅት አመራሮችን በሀገሪቱ ውስጥ ለተነሳው ህዝባዊ ዓመጽ በተለይም የተከሰተውን ብሔር ተኮር ግጭት መንስኤ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ አመራር ድክመት ነው ብለው እንዲቀበሉ የተለያዩ ስልትና ዘዴዎችን በመጠቀም እየጠረ ሲሆን ዓላማውም ጥፋተኝነትን አናዝዞ በምትካቸው አዲስ ለመተካት እንደሆነ ይነገራል።

ሁኔታውን በሁለቱ ድርጅቶች ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ የተነሳ ህወሃት ማንኛውንም መንገድና ሃይል በመጠቀም የሁለቱን ድርጅቶች ወቅታዊ ሚናን እና ህዝባዊ ተቀባይነትን የሚቀንስበትና ብሎም ይበልጥ የሚቆጣጠርበትን መደምደሚያ ውሳኔ ይዞ ይወጣል ተብሎ እየተጠበቀ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የአህዴድና ብአዴን ወሳኝ እርምጃ ብቻ የህወሃትን እቅድ እንዳይፈጸም ሊያግድ እንደሚችልም ይጠበቃል።

በአቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የሚመራው ኦህዴድና ብአዴን ድርጅት እራሱን ከህወሃት መራሹ ኢህአዴግ አባልነት ሙሉ በሙሉ የመለየት ውሳኔን እንዲወስኑ ይጠበቅባቸዋል።

ሁለቱ ድርጅቶች አሁን በያዙት ድርጅታዊ አቋምና ጥያቄ መሰረት ከህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ጋር በሃላፊነታቸው ይቀጥላሉ ወይም አብረው እንደከዚህ ቀደሙ ይጋዛሉ ብሎ መገመት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን የሚቻልም ጉዳይ አይደለም።

ሁለቱ ድርጅቶች ከሁለት አንዱን ለመምረጥ የተገደዱበት  ምእራፍ ላይ መድረሳቸውን እያየን ነው።

ላለፉት 27ዓመታት በህወሃት የበላይነት ሲጋዝ የነበረውን ኢህአዴግን ዛሬ በህወሃት እግር ተተክተው በአዛዥነት መምራት ካልቻሉ ይህን አቃምና ጥያቄ ይዘው በህወሃት የበላይነትና አዛዥነት ስር በሰላም ይቀጥላሉ ብሎ ማሰቡ አዳጋች ይሆናል።

በአንጻሩም የህዝብን ጥያቄ አንግበውና ህዝባቸውን ከሃላ አሰልፈው ከህወሃት ታዛዥነት እና ከኢህአዴግ አባልነት  ሙሉ በሙሉ መፋታት አሊያም የህዝብ ወገንተኝነታቸውን ጥለው የህወሃት አገልጋይነታቸውን ሙሉ በሙሉ ተቀብለው ለመቀጠል መወሰን ይኖርባቸዋል።

ህወሃትም ሆነ ህዝቡ በሁለት ቦታ ታማኝ የሚሆኑትን አመራሮች የሚፈልጉም ሆነ የሚያቅፉ ስላልሆኑ ድርጅቶቹ ከሁለት አንዱን የመምረጥ ግዴታ ላይ እንዳሉ ሊረዱት ይገባል።

ኦህዴድና ብአዴን በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ላይ ህወሃትን በድምጽ እናሸንፋለን ብለን እንደማይጠብቁ ቢታወቅም በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ህወሃት በድምጽ ብልጫ የማሸነፍ አቅምና ኔትወርክ አለኝ በማለት ለሁለቱ ድርጅቶች አጀንዳ ተንበርካኪ ለመሆን እንዳልተዘጋጀ ይታወቃል።

የሁለቱም ድርጅቶች በኢህአዴግ ውስጥ ሆነው የሚያደርጉት ግብግብ በየትኛውም ስሌትና ብዜት ተሸናፊ እንጂ አሸናፊ ስለማያደርጋቸው ማድረግ የሚገባቸው ወሳኝ እርምጃ እራሳቸውን ከስራ አስፈጻሚው ስብሰባ በማግለል አጀንዳቸውን ወደ ፓርላማ በመውሰድ እንደ የፓርላማው አብዛኛ አባልነታቸው ህወሃትን ሊያሸነፉት እንደሚችሉ ሊረዱ ይገባል።

የኢህአዴግን ህልውና እጅግ የሚፈልገው ከኦህዴድና ብአዴን ይልቅ ህወሃት እንደሆነ ሊዘነጋ አይገባም።

ኦህዴድም ሆነ ብአዴን ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ህልውና ወጥተው መኖር ቢችሉም ከሚያጡት ይልቅ የሚያገኙት ሀገራዊ፣ ድርጅታዊና ህዝባዊ ጥቅሞች እጅግ ከፍተኛ ነው።

በአንጻሩም የህወሃት ህልውና እና ጥቅም ከኢህአዴግ ህልውና ጋር የተቆራኘ ከመሆኑም በላይ የኢህአዴግ መፍረስ ለህወሃት የምጽዓት ቀን ያህል የህልውናው ማክተም ስለሆነ ኦህዴድና ብአዴን በትክክል የህዝቡን ጥያቄ ለማስተናገድ የወሰኑ ከሆነ ስለ ኢህአዴግ ድርጅታዊ ህልውና አንዳች ሳይጨነቁ ጥለው መውጣት ይገባቸዋል እላለሁ።
ቸር እንሰንብት!

- አስተያየታችሁን በኢትዮሚዲያ ኢ-ሜይል ወይም በግሌ teklu7@gmail.com ብላችሁ ልትልኩ ትችላላችሁ።

Ethiomedia.com
December 28, 2017